# በኢትዮጵያ ላይ የታወጀው የጅሃድ
# ጦርነት ቅዱስ ወይስ እኩይ?

ከብስራት ከበደ
ዩ. ኤስ. ኤ

እንደ የዓለም ዋንጫ፣ በየአራት ዓመቱም ሆነ በየአምስት፤ አገራችን ኢትዮጵያ የምታስተናግደው የወረራ ጦርነት፤ የእግዚአብሄር ቁጣ ይሆን ወይስ ዕድል? ይህ በኢትዮጵያችን ላይ የሚነጣጠረው እኩያዊ ሴራስ ጠንሳሹና መስራቹ ማን ይሆን? እስካሁን ድረስ መፍትሄ ያልተገኘለት ሴራስ በምን ዓይነት ዘይቤ መፈታት ይኖርበት ይሆን? ከላይ የተጠቀሱት ጥያቄዎች ህሊናዮ ላይ ብልጭ እያሉ ስለበጠበጡኝ ለአምባቢያን ያለኝን ሃሳብ ወርወር ላድርግ በሚል ሂሳብ ነው ይህቺን አጭር ፅሁፍ ለመክተብ የበቃሁት።

Holly War (ቅዱስ ጦርነት) የተባለው ምክንያትስ ለምን ይሆን? ለመሆኑ የጦርነት እኩይ እንጂ፤ የጦርነት ቅዱስስ የታየበት ዓለም የት ነው? ያም ሆነ ይህ በኔ አመለካከት፣ ጦርነት አውዳሚና ለብዙዎች ህልፈት ምክንያት እንጂ ቅዱስ ሆኖም አያውቅ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚ/ር አቶ መለስ ዜናዊ፤ ይህ በእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ኅብረት (አል-ጃምዓ አል-ሸርዕያ አል-እስላሚያ) ስር የተጠለለው አሸባሪ ቡድን በኢትዮጵያ ላይ ያወጀው ጦርነት፣ ግልፅና ወቅታዊ አደጋ ነው ብለውታል። እውነትም ግልፅና ወቅታዊ አደጋ ነው። ይህ በእስላማዊ ፍርድ-ቤቶች ኅብረት ጥላ ስር የተኀለተው አሸባሪ ቡድን፤ ባወጀው ጦርነት ላይ ለአንባቢያን መረጃ እንዲሆን ከአባቴ የወረስኩትን አንድ የወሎ ንጉስ የተናገሩትን ትምህርት ሰጪ ተረትና ምሳሌ ልጥቀስላችሁ።

ድሮ አገራችን ኢትዮጵያ በአዜዎች ስትተዳደር፣ ወሎ ከሸዋ፣ ትግራይም ከጎጃም ሌሎችም ክፍላተሃገራት እርስበርስ የሚግባቡ አልነበሩምና፣ አልፎ አልፎ ጦርነት

ይከሰት ነበር። ይሁንና እኚህ የወሎ ንጉስ በአንድ የውጭ ጋዜጠኛ ሲጠየቁ፤ "በወሎና በሸዋ፣ በሌሎችም ክፍላተ ሃገራት ደም መፋሰስ እየተከሰተ ነው። እርስ በርስ የሚያጣላችሁ ነገር ምንድነው?" ብሎ በአስተርጓሚ ሲጠይቃቸው፣ የወሎ ንጉስ ሲመልሱ፤ "ልጄ ከየትኛው አገር የመጣህ ጋዜጠኛ ነህ? ብለው ጠየቁት። ጋዜጠኛውም ሲመልስ፣ እኔ ከሃገረ ኢጣሊያ የመጣሁ ጋዜጠኛ ነኝ። ይህ የርስ በርሳችሁ ደም መፋሰስ አስገርሞኝ፤ ችግራችሁ ምንና ማን እንደሆነ ልዘግብ ነው የመጣሁት ሲል፣ አይ ልጄ! ይህ የርስ በርስ ደም መፋሰስ ብለህ የምትለው፣ የጓሮአችን ችግር ነውና ራሳችን እንወጣዋለን። ይሁንና የእውነት ጠሃፊም ጋዜጠኛም ከሆንክ፤ በ1896 ከኢጣሊያ ጋር ዓድዋ ላይ ያካሄድነውን ጦርነት ልንገርህና፤ አገርህ ሄደህ ላልሰማ አሰማ" አሉት ይባላል። ይህንን ምሳሌ ለማስታወስ ለምን ተገደድክ እንደምትሉኝ አልጠራጠርም። እናም ይህንን ምሳሌ የጠቀስኩበት አብይ ምክንያት፣ በኛ ላይ ጦርነት ያወጁትንና በእስላማዊ ፍርድቤቶች ኅብረት ጥላ ስር ያሉት ሽብርተኞች የእውነት ለአገራቸውና ለወገኖቻቸው ተቆርቋሪ፣ሃይማኖተኞች፣ጀግኖች፣ በጎና ታሪክ ሰሪዎች ከሆኑ፣ ባሉበት ከመራመድ አልፈው፤ በሰለጠነው ዘመን መንግስት አልባ የሆነችውን አገራቸው፤ ህዝባዊ መንግስት ማቋቋም፣ ዲሞክራሲና ሰላም ማስፈን፣ ልማትና እድገት ማፋጠን እንጂ በሰው አገር ላይ ጦርነት ማወጅ ለራሳቸውም ሆነ ለወገኖቻቸው የሚበጅ ተግባር አለመሆኑን ለመጥቀስ ነው።

እኛ ኢትዮጵያውያኖች፣ ከየትኛውም አቅጣጫ የሚሰነዘርብን የውጭ ወረራም ሆነ ትምክህት ማኮላሸት ባህላችን እንደሆነ አለም የሚገነዘበው ሃቅ ነው። ዛሬም ቢሆን በእስላማዊ ፍርድቤቶች ህብረት ስር ካለው ሽብርተኛ ቡድን የሚሰነዘርብንን ጥቃት ለመከላከል እንደማናቅማማ ከወዲሁ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ነው። እንዳውም የውጭ ወራሪ በሚዘምትብን ግዜ፤ የውስጥ ችግራችን ተቀርፎ፣ ህብረታችን ጎልብቶ፣ አንድነታችን ጠንክሮ የባዕድ ጠላት የምንገርፍበት አጋጣሚ በየወቅቱ ይከሰት እንደነበር የቅርብ ግዜ ትውስታችን መሆኑ አንዱና ዋነኛው ምስክር ነው። እኛም ከላይ እንደጠቀስኩት የባዕድ ወራሪ ማክሸፍና ማኮላሸት እንደ የዓለም የእግር ኳስ ዋንጫ ማስተናገድ ከጀመርን ዘመናት አስቆጥረናል። እናም ይህ አጉራ ዘለል የሽብርተኞች ቡድን አርፎ ለህገሩና ለወገኑ እድገትና ብልፅግና በጎ ነገር ማሰብ ቢጀምር ይሻለዋል እላለሁ።

በውጭም ሆነ በአገርቤት የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ዜጋ መገንዘብ ያለበት ጉዳይ ግን ይህ በእስላማዊ ፍርድ-ቤቶች ህብረት ስር የተጠለለው የቅዠትና የሽብር ቡድን የሚያውጀው ጦርነት፤ የሶማሊያ ወንድማማች ህዝብ እንደማይጨምር በግልፅ መቀመጥ ይኖርበታል ብል ማጋነኔ አይደለም። ያ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተባበሩት መንግስታት የፀጥታ ምክርቤት እንዳረጋገጠው፣ ይህ ሞቃዲሾ ውስጥ የሚንቀሳቀሰው የአሸባሪ ቡድን አስመራ ውስጥ መወለዱ ግልፅ ነው። እኩይ መካሪ ለሞት ያጋልጣል እንደተባለው ይህ የመረብ ማዶ ሰውዬ ያልተሳካለት እኩይ ተግባር በተዘዋዋሪ ለማሳካት ደፋ ቀና ቢልም የሌሎችን ዜጎች ህይወት አጥፍቶ ከመጥፋት በስተቀር በኢትዮጵያ ላይ የሚያስከትለው ተፅእኖ ቅንጣት ታህል ሊኖር እንደማይችል ሳይታለም የተፈታ ነው። ድሮስ በራስ የማይተማመን ሰው በሌሎች ዜጎች ህይወት መተማመን የሚያስገኘው ውጤት ይኖራልን? በሌሎች ዜጎች ህይወት መቀለድ ከንቱ ህልም ከመሆን አልፎ አዲስ ግኝት የለውም።

ካሁን በፊት በሚድያ እንደተዘገበው፣ በጎረቤት አገር ሶማሊያ ሰላም መስፈን ለመላው የአፍሪካ ቀንድ መረጋጋት በጣም ወሳኝ ባይሆንም ታላቅ አስተዋፀኦ እንዳለው በኢትዮጵያ መንግስት በኩልም ጥረት ሲደረግ መቆየቱ ማንም የሚገነዘበው ነው። አሁንም ቢሆን ከማንኛውም የአፍሪካ ህዝብ በላይ ሰላምና መረጋጋት የናፈቀ ህዝብ ቢኖር የሶማሌ ህዝብ ነውና፤ ለዚሁ ለወንድማማች የሶማሊያ ህዝብ ሰላምና ዲሞክራሲ መስፈን ሁሉም የዓለም ህዝቦች የበኩላቸው አስተዋፀኦ ያደርጉ ዘንድ ሰላም፣ ፍቅር አንድነትና ዕድገት ለሶማሊያ ህዝብ መልካም ምኞቴ በመግለፅ ፅሁፌ እዚሁ ላይ እቋጫለሁ።

ቸር እንሰንብት!!